# ወልድ ዋሕድ ክርስቶስ

## ጥያቄ፦ ወልድ ዋሕድ ማን ነው?

ወልድ ዋሕድ ተብሎ የተጠራው፣ የአብ አካላዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ነው።

## ጥያቄ፦ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ለምን ወልድ ዋሕድ ተብሎ ይጠራል?

ወልድ ዋሕድ ማለት አንድ ብቻ የሆነ ልጅ ማለት ነው፤ ስለዚህ አካላዊ ቃል እምቅድመ ዓለ ም (ዓለም ከመፈጠሩ በፊት) ከእግዚአብሔር አብ ባሕርይ ዘእም ባሕርይ፣ አካል ዘእምአካል ስለ ተወለደ (ስለ ተገኘ)፣ እንደዚሁም ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ «ተገኘ፣ ተወለደ» ተብሎ የሚነገርለት ሌላ ስላልነበረ፣ ስለሌለና ወደ ፊትም ስለማይኖር፣ እርሱ ብቻ ብሕትወ ል ደት (ባሕታዌ ልደት) እንደሆነ ለዘላለም ስለሚኖር፣ «ወልድ ዋሕድ» ይባላል። አካላዊ እግዚአ ብሔር ቃል «ወልድ ዋሕድ» እንደሚባል ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ሲመሰክር፣ «ለእግዚአብ ሔርሰ አልቦ ዘርእዮ ግሙራ፣ አላ ወልድ ዋሕድ ዘሀሎ ውስተ ሕፅነ አቡሁ ውእቱ ነገረነ» ብ ሎአል። ይኸውም፣ «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ ክብር ያለ አንድያ (አንድ ብቻ የሆነ) ልጁ ነገረን እንጂ» ማለቱ ነው (ዮሐ.፩፥፲፰)።

ቀጥሎም ይህ ወንጌላዊ እግዚአብሔር አብ ዓለምን ለማዳን ሲል ወልድ ዋሕድን (አንድያ ልጁ ን) ወደ ዓለም እንደ ላከው ሲመሰክር፣ «እስመ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም እስከ ወልዶ ዋ ሕደ መጠወ ወወሀበ ቤዛ ለኵሉ»፤ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እ ንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ለዓለም ቤዛ እንኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና» ብሎአል። ከዚያው አያይዞም እንዲህ ሲል አስረድቶአል፤ «ዓለም በልጁ እንዲድነ ነው እንጂ ዓለምን እንዲፈረድበት፣ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም አላከውምና፤ በእርሱ የ ሚያምን አይፈረድበትም፣ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱበእግዚአብሔር ልጅ ስም ሰላላመነ፣ አሁን ተፈርዶበታል» (ዮሐ.፫፥፲፮-፲፱)። በተጨማሪም በመጀመሪያ መልእክቱ እንዲህ ብሎአል ፤ «ወበዝንቱ ተዐውቀ ፍቅሩ ለእግዚአብሔር ላዕሌነ፣እስመ ለወልዱ ዋሕድ ፈነዎ ውሰተ ዓለም ከመ ንሕየው ቦቱ፤ በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ታወቀ (ተገለጠ)፤ በእርሱ እንድን ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና» (፩ኛ ዮሐ.፬፥፱)።

## ጥያቄ፦ አካላዊ ቃል ዓለምን ለማዳን በኋለኛው ዘመን ከቅድሰት ድንግል ከሥጋዋ ሥ ጋ፣ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ (ተዋሕዶ)፣ ከኃጢአት በስተቀር ፍጹም ሰው ሆኖ ከ ተወለደ በኋላ ወልድ ዋሕድ ተብሎ ይጠራልን?

አዎን፤ ወልድ ዋሕድ እየተባለ ይጠራል፤ ምክንያቱም እምቅድመ ዓለም ከአብ ባሕርይ የተወለ ደው እርሱ ነው፤ በኋለኛው ዘመንም ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደው እርሱ ነው ። እርሱ ራሱ በመለኮት የአብ የባሕርይ ልጅ ነው፤ ወዲህም እርሱ ራሱ በተዋሐደው ሥጋ የቅ ድስት ማርያም ልጅ ነው። ከሦስቱ አካላት አንዱ እርሱ፣ በአንድ ጊዜ ወልደ አብ ወልደ ማር ያም ነው።

## ጥያቄ፦ አካላዊ ቃል ስንት ጊዜ ተወለደ?

ሁለት ጊዜ ብቻ ተወለደ።

፩ኛ. እምቅድመ ዓለም በመለኮት ከአብ ባሕርይ ዘእም ባሕርይ፣ አካል ዘእም አካል ተወልደ፤

፪ኛ. አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና ተወለደ።

ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ሁለት ልደታት ብቻ እንዳሉት የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በየድርሳናቸው አስፍተው መስክረዋል። ከእነርሱም አንዱ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፣ ሳዊርያኖስ ዘገብሎን (ዘኤላ)፣ አጺፋንዮስ ዘቆጵሮስ፣ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ ያስተማሩትን እንጠቅሳለን፦

፩ኛ. ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ እንዲህ ሲል መስክሮአል፤ «ዳግመኛ ለወልደ እግዚአብሔር ሁለት ልደታት እንዳሉት እናምን ዘንድ ይገባናል፤ አንደኛው፣ ከዘመን ሁሉ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደው ልደት ነው፤ ሁለተኛው፣ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በኋላ ዘመን የተወለደው ልደት ነው» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፻፲፯፣ ቀኍ.፮)።

፪ኛ. ቅዱስ ሳዊርያኖስ ኢጺስቆጶስ ዘሃገረ ገብሎን ደግሞ እንዲህ ሲል ያስተማረውን እንጠቅሳለን፤ «በማይመረመር ልደት በተወለደው በአካላዊ ቃል እናምናለን፤ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ፣ ዓለምን አሳልፎ ለዘላላም የሚኖር ቀዳማዊ ደኃራዊ እርሱ ነው።ዳግመኛም ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ በምድር ላይ ከቅድስት ደንግል ማርያም እርሱ በሥጋ ተወለደ፤ በዚህ ዓለም የተወለደው ሰው ሁሉ ከዳግማዊ አዳም ዳግመኛ ይወለድ ዘንድ (ያምን ዘንድ) ይገባዋል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ቃል ነው» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፻፳፭፣ ቀኍ.፪-፫)።

፫ኛ. ቅዱስ ኢጺፋንዮስ ዘቆጵሮስም ስለዚሁ ሲመስክር፣ «አብ ጥንት፣ ፍጻሜ የሌለውን ቃል ዓለምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ወለደው፤ በኋላ ዘመንም በግብረ መንፈስ ቅዱስ (በመንፈስ ቅዱስ ጥበብ) ንጽሕት ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ተወለደ» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፻፴፯፣ ቀኍ.፲፩)።

፬ኛ. ሳዊሮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘአንጾኪያም እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «ሁለት ልደት እንዳለው በእግዚአብሔር ቃል እንዲሁ ልናምን ይገባናል፤ አንዱ፣ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደው የማይመረመር ልደት ነው፤ ሁለተኛውም፣ ያለ አባት የተወለደው የማይመረመር፣ የማይነገር ልደት ነው» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ ፫፻፶፯ ቀኍ.፳)።

ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ፣ በቀዳማዊ ልደቱ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን ራሱ እግዚአብሔር አብ፣ ፩ኛ. በዮርዳኖስ፣ ፪ኛ. በደብረ ታቦር፣ «የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት» ሲል የባሕርይ ልጅነቱን መስክሮለታል (ማቴ.፫፥፲፯፤ማቴ.፲፯፥፭-፯)። እንደዚሁም ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ያለ አባት ከንጽሕት ቅድስት ድንግል በሥጋ መወለዱን ወንጌላውያኑ መስክረዋል (ማቴ.፩፥፲፱-፳፭፤ ሉቃ.፩፥፳፯-፴፰፡ ፪፥፯)።

## ጥያቄ፦ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ፣ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የባሕርይ ልደታቱ ሌላ ሦስተኛ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ተወለደ ማለት ተገቢ ነውን?

በፍጹም አይገባም። ይህ አባባል የዐላውያን ማለት የመናፍቃን ትምህርት ነውና የተወገዘ ነው።

## ጥያቄ፦ በጸጋ መወለድ ወይም የጸጋ ልጅ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

በመሠረቱ፣ ጸጋ ማለት ሀብት፣ ብዕል፣ ሰጦታ፣ ገንዘብ ማለት ነው፤ በዚሁ መሠረት ሀብትን ወይም ስጦታን በመቀበል፣ የስጦታው ወይም የሀብቱ ተቀባይ ለስጪው የጸጋ ልጅ ይባልለታል። ሀብትን በመውረስ ወይም ስጦታን በመቀበል የሀብት፣ የጸጋ፣ የስም ልጅ ይባላል፤ ይኸውም ከአባት እናት ሳይወለድ ሀብት በመቀበል (በመውረስ)፣ ወይም ስጦታን በመቀበል ብቻ ልጅ ተብሎ ሲጠራ የጸጋ ልጅ ይባላል። ለምሳሌ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በመቀበል የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ። ሰለዚህ ቅዱስ ዮሐንስ ሲመስክር፣ «የእርሱ ወደ ሆኑት መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም፤ ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው፣ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም፣ ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም» ሲል አስረድቶአል (ዮሐ.፩፥፲፩-፲፫)። ራሱ ጌታችንም ምስጢሩን ለኒቆዲሞስ ሲያስረዳው፣ «እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ብሎታል። ይኸውም በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ መንግሥተ ስማያት ሊገባ አይችልም ሲለው ነው (ዮሐ.፫፥፭-፯)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፣ በጌታ በኢየሱስ ያመኑ ክር

ስቲያኖች ከመንፈስ ቅዱስ በጸጋ ተወልደው የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ስለ መጠራታቸው እንዲህ ሲል መስክሮአል፤ «እግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለ ፍርሐት የባርነት መንፈስ አልተቀበላችሁም። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል»(ሮሜ.፰፥፲፬-፲፮)።

የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ማለት አዳምና ሔዋን በኃጢአት ምክንያት ሞት ሳይፈረድባቸው በፊት በንጹሕ ባሕርይ ሳሉ ልጅነትን ከእግዚአብሔር ተቀብለው እንደ ነበር የታወቀ ነው፤ ይኸውም በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች ይባሉ ነበር ማለት ነው። በኃጢአት ሲወድቁ ግንየጸጋ ልጅነታቸው ሲወሰድባቸው ሁለቱም ከእግዚአብሔር ጸጋ ታረዙ፤ ራቁታቸውንም እንደሆኑ ተገነዘቡ፤ከዚያም ዕርቃነ ሥጋቸውን በበለሱ ቅጠል ሸፈኑ (ዘፍ.፫፥፯)፤ ነገር ግን አዳምና ልጆቹ የእግዚአብሔርን ሕግ ተላልፈው ያስወሰዱትን የጸጋ ልጅነት፣ በኋላ ዘመን እግዚአብሔር ወልድ የአዳምና የአብርሃም ወገን ከሆነችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ከኃጢአት በስተቀር ፍጹም ሰው ሆኖ በሥጋው የአዳም፣ የአብርሃም ልጅ ተብሎ በመጠራት፣ በጥምቀትና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለአዳምና ለዘሮቹ መልሶላቸዋል። ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ የሰው ልጅ ሲባል፣ የሰው ልጆች ደግሞ በጸጋ እግዚአብሔር ልጆች ተብለው እንዲጠሩ ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል (ዮሐ.፩፥፩)።

ሰዎች ክርስቶስን በማመን ከጥምቀትና ከመንፈስ ቅዱስ ሁለተኛ ሲወለዱ በጸጋ እግዚአብሔር ልጆች እንደሚሆኑ በርከት ያሉ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አስተምረዋል። ከእነርሱም አንዱ ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ ለማስረጃ እንጠቅሳለን። ሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ በ፳፰ኛው መልእክቱ ስለዚሁ ሲያትት፣ «እኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች (ባሮች)፣ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ የአገልጋዮች ጌታ ወልደ እግዚአብሔር የአገልጋዩን የአዳም ልጅ ተብሎ ተጠራ፤ የመዋቲው የአዳም ልጆች የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ፣ የአዳም አምላክ ወልደ እግዚአብሔር የአዳም ልጅ ሆነ፤ ነገር ግን እርሱ (ቃል) የአብ የባሕርይ ልጅ ሲሆን፣ እኛ ግን በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል» በማለት አስረድቶአል። በሌላው መልእክቱም፣ «ወበእንተ ዝንቱ ተዋረሰ ስብእ፣ ሱታፌ ዝንቱ መንፈስ በሀብቱ፣ ወተሰምዩ ስብእ ደቂቀ እግዚአብሔር፤ ስለዚህ ሰው በልጅነቱ (በጸጋ ልጅነት)ከመንፈስ ቅዱስ አንድነት ገንዘብ አደረገ፤ ሰዎችም በጸጋው የእግዚአብሔር ልጆች ተባሉ»(ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፹፱ ቍ.፴፮)።

ስለዚህ ሰው ክርስቶስን በማመን በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ሲወለድ፣ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅ እንደሚሆን የታወቀ ሲሆን፣ ለወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ግን የአብ የባሕርይ ልጅ ከመሆኑ በስተቀር «የእግዚአብሔር አብ የጸጋ ልጅ ሆነ» ተብሎ ሲነገርለት ቀርቶ ሊታሰብ የማይገባ ነው፤ ይህን የመሰለ ትምህርት ከዐላውያን (ከመናፍቃን) በቀር ማንም አያሰበውም። ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ፣ አምላክ ወልደ አምላክ ስለሆነ፣ ለፍጡራን ሁሉ ጸጋን የሚያድል የጸጋ ባለቤት ነው። እርሱ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን አትረፍርፎ የሚሰጥ የባሕርይ አምላክ መሆኑን በማረጋገጥ፣ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንዲህ ይላል፤ «እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀበልን፤ በጸጋም ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና፤ ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፤ ጸጋና እውነት (ጽድቅ) ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ»(ዮሐ.፩፥፲፮-፲፯)።

**ጥያቄ፦«ክርስቶስ በቅብዐት ወይም በጸጋ ከመንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ ተወልዶ የእግዚአብሔር አብ የጸጋ ልጅ ሆነ» ብለው ያስተማሩት እነማን ነበሩ?**

ከአንጾኪያ ትምህርት ቤት ሠልጥነው የወጡ፣ ጳውሎስ ሣምሳጢና ዲኦዶር ዘጠርሴስ፣ ፌኦዶር ዘሙፑስኢስቲያና ንስጥሮስ ዘቁስጥንጥንያ፣ እንዲሁም እንድርያስ ዘሣምሳጢያና ፌኦዶሪት ዘሲረስ የጸጋንና የኅድረትን ትምህርት ማስተማርና ማስፋፋት ሞክረው ነበር።

**ጥያቄ፦ መናፍቁ ጳውሎስ ሣምሳጢ ምን ብሎ አስተማረ?**

ጳውሎስ ሣምሳጢ ምስጢረ ሥላሴ በመካድ፣ «የእግዚአብሔር አካልና ገጽ አንድ ነው፤ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ቢባልም በስም ነው እንጂ በገጽና በአካል ሦስት አይደለም፤ ቃል ወይም ወልድ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር አብ አካል ገጽ የላቸውም፤ ወልድና መን

ፈስ ቅዱስ አካልና ገጽ ሳይኖራቸው የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ናቸው…» እያለ ያስተምር ነበር።

ምስጢረ ሥጋዌን በሚመለከትም፣ መናፍቁ ጳውሎስ ያስተማረው እንዲህ የሚል ነው፤ «ኢየሱስ ክርስቶስ የናዝሬት ሰው ከነበረችው ከድንግል ማርያም ተወለደ። ነገር ግን እርሱ እግዚአብሔር የመረጠው ቅዱስ ሰው ነው እንጂ ከሰማይ የወረደ አምላክ አይደለም። ኢየሱስ በባሕርዩ ሰው እንጂ አምላክ አይደለም፤ ነገር ግን ሰለ መልካም ሥራውና ስለ ንጽሕናው በእናቱ ማኅፀን ና በዮርዳኖስ ወንዝ ቃለ እግዚአብሔር በጸጋና በክብር አደረበት፤ አደረበት ሲባል በነቢያትና በ ቅዱሳን ሰዎች እንዳደረባቸው በርሱም እንደ እነርሱ ማለት አይደለም፤ነገር ግን በእርሱ ላይ በ ብዙ እጥፍ በፍጹምነት አደረበት እንላለን እንጂ። ሰለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስና ከሰማይ የወረደ ው ቃለ እግዚአብሔር በክብርና በፈቃድ አንድ ስለሆኑ (ሰለ ተጣመሩ)፣ ኢየሱስ በጸጋ የእግዚአ ብሔር ልጅ ተባለ። በወንጌል የተዘረዘሩት አስደናቂ ሥራዎች፣ ተአምራት የተፈጸሙት በኢየሱ ስ ክርስቶስ ላይ ባደረው ከሰማይ በወረደው በቃለ እግዚአብሔር ኃይል ነበር….» እያለ ያስተም ር ነበር።

ይህንን አጸያፊ ትምህርት የሰሙ፣ በዘመኑ የነበሩት ኦርቶዶክሳውያን ኤጲስ ቆጶሳት በ፪፻፷፬፣ በ፪፻፷፷፣ በ፪፻፷፱ ዓ.ም ሦስት ጊዜ በአንጾኪያ ከተማ ጉባኤ አድርገው ትምህርቱን በጥንቃቄ ከመረመሩ በኋላ፣ የሐዋርያትን ትምህርት የሚቃረን ሆኖ ሰላገኙት እርሱንም ጠይቀውት አልመ ልስም ስላላቸው፣ ተስማምተው አውግዘውታል። ቀደም ብሎም እነዚያ አባቶች፣ መናፍቁን ከክ ሕደቱ እንዲመለስ ደጋግመው መክረውት ነበር፤ ነገር ግን በፍጹም የማይመለስ ሆኖ ሰላገኙት ከ ሹመቱ ሽረውና አውግዘው ከቤተክርስቲያን ለይተውታል። ጳውሎስ ሣምሳጢንና ክሕደቱን ካወገ ዙት ኤጲስ ቆጶሳት መካከል ቅዱስ ዲዮናስዮስ ዘእስክንድርያና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ገባሬ ተአምር ፣ ዲዮናስዮስ ዘሮም ይገኙባቸዋል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚነበበው፣ መናፍቁ ጳውሎስ ሣምሳጢ የክርስቶስ አምላክነት በመካድ፣ በአሥር አሉታዊ መጠይቅና በአሥር አንቀጽ የተጻፈ ትምህርቱን በቅዱስ ዲዮናስዮስ ዘእስክንድርያ አድራሻ በመላክ የሐዋርያትን እምነት ለማስተባበ ል ሞክሮ ነበር፤ ነገር ግን ቅዱስ ዲዮናስዮስ ዘእስክንድርያና ኤጲስ ቆጶስ ኖቮቲያን የጳውሎስ ሣምሳጢ ትምህርት ፍጹም ውሸትና ከንቱ መሆኑን በመግለጽ የጻፉትን የመልስ ጽሑጽ መናፍቁ አፉን እንዲይዝ አድርገውታል። ከብሉይና ከሐዲስ ጠቅሰው በሰፊው ባዘጋጁት የመልስ ጽሑፍ ፣ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ምንታዌ የሌለበት፣ ወልድ ዋሕድ፣ የባሕርይ አምላክ መሆኑን በሚገባ መስክረዋል።

በአራተኛው ክፈለ ዘመን የተነሡ የቤተክርስቲያን ሊቃውትም፣ የጳውሎስ ሣምሳጢና ከተከታዮ ቹ ትምህርት ፍጹም ሐሰትና ከንቱ መሆኑን ገልጸው፣ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ምንታዌ የ ሌለበት አንድ ወልድ ዋሕድ የባሕርይ አምላክ መሆኑን አረጋግጠዋል፤ በተለይም ቅዱስ ኤጲፋ ንዮስ ዘቆጵሮስ፣ «ጳውሎስ ሣምሳጢና ተከታዮቹ በስም ክርስቲያኖች ከመባላቸው በስተቀር፣ጌታ ችንን ከስቀሉት ከቤተ አይሁድ በምን ይለያሉ? በምንም አይለዩምና ተወግዘውና ተረግመው ከቤ ተ ክርስቲያን መለየታቸው የሚገባ ነው» ሲል ጽፎአል።

የጳውሎስ ሣምሳጢ ደቀ መዛሙርት የነበሩት ዲኦዶር ዘጠርሴስ፣ ፌኦዶር ዘሙቍሲአስቲያና ንስ ጥሮስ ዘቁንስጥንጥንያ፣ ፊኦዶሪት ዘሲረስና ሌሎች የአንጾኪያ ትምህርት ቤት መናፍቃን፣ ጳው ሎስ ሣምሳጢ የመሠረተውን የኅድረትንና የምንታዌን ትምህርት በተለያየ ዘዴ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለማስፋፋት ሞክረው ነበር፤ ነገር ግን በየጊዜው የተነሡ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በጉባ ኤ፣ እንዲሁም በግል መናፍቃኑ በማሳፈር ትምህርታቸውን አጥብቀው አውግዘዋል። ከእነርሱም መካከል ለማስረጃ ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥለን እንጠቅሳለን፦ ምንታዌነትንና ኅድረትን በመቃወም ቅ ዱስ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት እንዲህ ሲል አውግዞአል፤ «ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ የእግዚ አብሔር ልጅ ሌላ ነው፤ ከማርያም የተወለደው ሌላ ነው የሚል፣ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ራሱ እንደሆነ፣ ቀዳማዊም፣ ደኃራዊም ያው አንዱ ብቻ እንደሆነ፣ በኋላ ዘመንም ከማርያም ሥጋን የነሣው እርሱ እንደሆነ የማያምን ቢኖር ውጉዝ ይሁን» ሲል ጽፎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ. ፭፻፶፬ ቍ.፲፯)። ቀጥሎም እግዚአብሔር ቃል እንደ ዕሩቅ ብእሲ (እንደ ፍጡር)፣ ከነቢያትም እንደ አንዱ ጸጋብ ተቀበለ የሚል፣ ከድንግል ነፍስንና ሥጋን ነሥቶ እንደ እኛ ፍጹም ሰው እን ደሆነ፣ በቤተልሔም እንደ ተወለደ፣ በናዝሬት እንደ ሕፃናት በየጥቂቱ እንደ አደገ፣ ሠላሳ ዘመ ን ሲሞላው በዮርዳኖስ እንደ ተጠመቀ፣ እንደ ተጻፈ፣ አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ እን

ደ መስከረለት የማያምን ቢኖር ውጉዝ ይሁን» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፭፻፶፭ቀ.፲፱) ። በተጨማሪም ይህ አባት ስለዚሁ ሲያስረዳ፣ «የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ የወረደ ነው፤ ከመለኮቱም ጋር በቅድምና የነበረ ነው የሚል፤ ሥጋ በቅድምና በነገረ በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠረ የማያምን፣ ቃልም በኋላ ዘመን በራሱ ፈቃድ፣ ባባቱ ፈቃድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ራሱን ዝቅ አድርጎ ሰው እንደ ሆነ፣ እንደ ተጻፈም የተገኘ የአዳምን ባሕርይ እንደ ነሣ (እንደ ተዋሐደ) የማያምን ቢኖር የተወገዘ ይሁን» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ገጽ.፭፻፶፮ ቀ. ፳፩ ክፍል ፲፩)።

ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያም፣ ምንታዌንና ኅድረትን በመንቀፍ ሲያስተምር፣ «አንዱ ከእግዚአብሔር የተገኘ የባሕርይ አምላክ ነው፤ ለእርሱ እንሰግዳለን፤ ሁለተኛው ከማርያም የተገኘ ሰው ነው፤ ለእርሱ አንሰግድም አንልም። እርሱ ከሰው ቢወለድም በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለምና፤ አስቀድሜ እንደ ተናገርኩ እርሱ ከእግዚአብሔር የተገኘ እግዚአብሔር ነው ያለ ውነው እንጂ» ሲል አስረድቶአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ ፹፰፣ ቀ.፬)።

በተጨማሪም ይህ ቅዱስ አባት፣ ሰለዚሁ ሲያስረዳ፣ «ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነው፤ እርሱም የባሕርይ አምላክ ነው፤ መለኮት ያደረበት በጸጋ የከበረ አይደለም፤ ሥጋን በመንሳት ሰው የሆነ እርሱ ብቻ ነው፤ በመለኮት የእግዚአብሔር ልጀ ነው፤ እርሱ አምላክ ነው፤ እርሱ ወልድ አንድ ብቻ ነው» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፹፱)።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስም፣ «ቃለ እግዚአብሔርና ኢየሱስ ክርስቶስ» ብለው የረከሰውን የምንታዌ ትምህርት (የሁለትነትን ትምህርት)ያስተማሩትን መናፍቃን በመገሠፅ እንዲህ ሲል አስተምሮ አል፤ «የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ (ማቴ.፫፥፲፯)። ይህ አንዱ ሁለት አይደለም፤ ልጄ ነው ያለው ሌላ፣ ከማርያም የተወለደው ሌላ አይደለም፤ በበረት የተወለደው ሌላ፣ ሰብአ ሰገል የሰገዱለት ሌላ አይደለም፤ የተጠመቀው ሌላ አይደለም፤ ጥምቀት የሚሻው ሌላ አይደለም፤ በእርሱ ህልው ሆኜ ልመለክበት የወደድኩት ልጄ ነው ያለው ነው እንጂ» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ. ፻፳፣ ቀ.፲፬)።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ቴኦሎጎስም (ነባቤ መለኮት) ወልድ ዋሕድ ክርስቶስን ሁለት አድርገው ያስተማሩትን መናፍቃን ሲያወግዝ፣ እንዲህ ብሎአል፤ «አንዱ ከእግዚአብሔር አብ፣ አንዱ ከድንግል ማርያም ብሎ ሁለት ወልድ የሚል፣ ከእግዚአብሔር የተወለደው፣ ከድንግልም የተወለደው አንድ አይደለም የሚል ቢኖር፣ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ካዘጋጀላቸው ልጅነት (የጸጋ ልጅነት) ይለይ» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፭፻፹)።

በተለይም፣ «ክርስቶስ የፍጹምነት (የትሩፋት) ሥራ በመሥራቱ በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ ተባለ »ብለው ያስተማሩትን መናፍቃን ሲያሳፍር፣ «ከጥምቀት በኋላ ፍጹም ሥራ ሠርቶ፣ ወይም መናፍቃን በረከሱ መጻሕፍቶቻቸው እንደሚናገሩት፣ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላወልድ መሆንን፣ ወልድ መባልን ተገባው የሚል ቢኖር ውጉዝ ይሁን» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፭፻፹፩) ። የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ቄርሎስም፣ መናፍቃኑን በመዝለፍ ያስተላለፈው ውግዘት እንዲህ የሚል ነው፤ «ክርስቶስ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው እንጂ የባሕርይ አምላክ አይደለም ብሎ ደፍሮ የሚናገር ስው ቢኖር፣ ሰው የሆነው፣ እንደኛም ሥጋን ነፍስን የተዋሐደው ቃል ፣ አንድ ብቻ የሆነ የባሕርይ ልጅ እንደሆነ የማያምን ቢኖር ውጉዝ ይሁን፤ ከአብ የተወለደው የእግዚአብሔር ቃል ለክርስቶስ ፈጣሪው ነው፤ ወይም ጌታው እንደሆነ የሚናገር ቢኖር፣ መጽሐፍ እንደ ተናገረ፣ ቃል ሥጋ እንደሆነ፤ እርሱ አምላክም ሰውም እንደሆነ የማይናገር ቢኖር ውጉዝ ይሁን፤ የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ በሚባል ሰው አድሮ ሥራውን እንደሚሠራ፣ ያንድነት ክብርም በኅድረት እንደ ተሰጠው፣ ከእግዚአብሔር ቃልም የተለየ እንደሆነ የሚናገር ሰው ቢኖር ውጉዝ ይሁን» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፱፻፸፹ ቀ.፵፯፡፵፰)።

## ጥያቄ፦ከዚህ በላይ እንደ ተመለከተው፣ ቅዱሳን የቤተክርስቲያን አበው ስም ሳይጠቅሱ ያወገዟቸው መናፍቃን እነማን ናቸው?

ቅዱሳን አባቶች ስማቸው ሳይጠቅሱ ያወገዟቸው መናፍቃን ቀደም ብለን እንደ ገለጽነው ጳውሎስ ሣምሳጢና ተከታዮቹ ናቸው። ከእነርሱም ዋና ዋናዎቹ ዲኦዶር ዘጠርሴስ ፌኦዶር ዘሙፑሲኢስቲያስ፣ ንስጥሮስ ዘቁስጥንጥንያ፣ እንድርያስ ዘሳምሳጢያ፣ ፊኦዶሪት ዘሲረስ ናቸው። የእነዚህ ሁሉ ትምህርታቸውና እምነታቸው ምንታዌና ኅድረት ነው።

## **ጥያቄ፦ ምንታዌ ማለት ምን ማለት ነው?**

ተመንተወ መንታ ሆነ ካለው የግእዝ ቃል ምንታዌ የተባለው ቃል ይገኛል፤ ፍችውም መንታነት፣ ሁለትነት ማለት ነው። ፈረንጆቹ ዱአሊዝም ይሉታል። በዚሁ መሠረት የአንጾኪያ መናፍቃን፣ ወልድ ዋሕድ ክርስቶስን ሁለት ነው ብለው በማመን፣ «ወልድ ዋሕድ የተባለ ቃለ እግዚአብሔርና ኢየሱስ ክርስቶስ የተለያዩ አካላት ናቸው፤ አንደኛው ሰማያዊ፣ ሌላው ምድራዊ፣ አንደኛው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ፣ ሁለተኛው የማርያም ልጅ....» በማለት ሐዋርያት ያወገዙትን የሁለትነት፣ የመንታነት ማለትም የምንታዌን ትምህርትማስተማር ሞክረው ነበር፤ ነገር ግን ተወግዘው ከቤተክርስቲያን ተለይተዋል።

## **ጥያቄ፦ ኅድረት ማለትስ ምን ማለት ነው?**

ኅድረት ማለት፣ ማደር መኖር ማለት ነው። ይህም መናፍቃኑ የምንታዌ ትምህርታቸውን ለመግለጽ የተጠቀሙበት ቃል ነው። «ቃለ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋ በክብር ስላደረበት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋና በክብር ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ተጣምሮ አንድ ሆነ» የሚል ይህ የተወገዘና አጸያፊ ባህል (አባባል) ኅድረት ይባላል። የሐዋርያት ቤተክርስቲያንም፣ ይህንን የምንታዌ የኅድረት ትምህርት በየጊዜው በጉባኤ አውግዛዋለች፤ እኛም እናወግዛለን።

## **ጥያቄ፦ከእግዚአብሔር አብ የተወለደው እርሱ ራሱ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ አንድ ወልድ ዋሕድ መሆኑ የሚያረጋግጥ ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላልን?**

አዎን፤ ይህን እውነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ እጅግ በርከት ያለ ስለሆነ፣ በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ማቅረብ ወይም መጥቀስ ያስቸግራል። ነገር ግን መጻሕፍተ ብሉያትና መጻሕፍተ ሐዲሳት በሙሉ ወልድ እግዚአብሔር ክርስቶስ፣ ምንታዌ የሌለው አንድ ብቻ መሆኑን ይመስክራሉና እነርሱን ልብ ብሎ መመልከት ይገባል።

የቤተክርስቲያን ሊቃውንትም፣ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም» ባለው መሠረት፣ ከሰማይ የወረደውና ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው፣ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ የተጠመቀውና በገዳመ ቆሮንቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት የጸመው፣ የተራበው፣ የተጠማውና ኅብስቱን አበርክቶ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ርኁባንን ያጠገበው እርሱ ብቻ መሆኑንመስክረዋል (ዮሐ.፫፥፲፫)።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘኑሲስ፣ የምንታዌ መምህራን የሆኑትን መናፍቃን በመገሠፅ እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «የተአምራትን ሥራ ለአንዱ ብቻ፣ የድካምን ሥራ ለአንዱ ብቻ ሰጥተህ አትናገር፤ ያም ይህን ለአንድ ለእርሱ ብቻ ነው እንጂ፤የአምላክነት ሥራ ሁሉ ገንዘቡ ነው፤ መከራን መቀበል ገንዘቡ ነው፤ እርሱ አንድ ብቻ አምላክ እንደ መሆኑ ተአምራት ያደርጋል፤ ሰውም እንደ መሆኑ መከራን ይቀበላል» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፪፻፩-፪፻፪፣ ቍ.፳፯-፳፰)። በተጨማሪም ይህ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ያስተማረውን ከዚህ ቀጥለን እንመልከት፤ «ሁለት ግብራት ለእርሱ (ለወልድ ዋሕድ) አንድ እንደ ሆኑ (እንደ ሆኑለት) አየህን? ሰው የሆነ አምላክ እርሱ ነው፤ አንድ ነው፤ ሁለት አይደለም፤ ፈጣሪ መለኮቱን ፍጡር ወደ መሆን አልለወጠውም፤ መችም መች አንድ ብቻ ነው፤ ሁለት አይደለም። የተገዠ ባሕርይን የተዋሐደው፣ በእርሱ ትሕትና እኛ እንከበር ዘንድ የተዋረደው እርሱ ነው፤ ህማማችንን የታገሰ፣ ደዌያችንን የተሸከመ፣ በደላችንን የተቀበለ፣ ሰለ እኛ የማያልፍ የማይለወጥ መሥዋዕት አድርጎ ራሱን ያቀረበ፣ የማይሻር የማይለወጥ ካህን እርሱ ነው፤ የሚሠዋ በግ እርሱ ነው፤ የሚሠዋ ካህን እርሱ ነው፤ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋርም መሥዋዕት የሚቀበል እርሱ ነው። በፈቃዱ መከራን የተቀበለ፣ መከራንም ሁሉ የታገሠ እርሱ ነው፤ እንደ በግ ሊሠዋ መጣ

፤ በግ በሚሸልተው ፊት እንዳይናገር አልተናገረም፤ በነገሩም ሐሰት አልተገኘበትም»(ኢሳ.፶፫፥፯-፱፤ ፩ጴጥ.፪፥፳፩-፳፭፤ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ፻፳፮ ቁ.፳፬-፳፭)።

ቅዱስ ፕሮክልዮስ (ኤራቅሊስ) ሊቀ ጳጳስ ዘቁንስጥንጥንያም፣ ወልድ እግዚአብሔር ክርስቶስ ምንታዌ የሌለበት አንድ ብቻ መሆኑን ሲያስረዳ፣ «አክሊለ ሦክ ደፍቶ የሞትን ሥልጣን ፍርድ አጠፋ፤ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ ሳለ ከመንበሩ አልተለየም፤የባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ አልተለየም፤ በምድር እንደ በደለኛ ሲዝቱበት፣ በሰማይ ቅዱስ ምስጋናውን ይናገሩለት (ያቀርቡለት) ነበር፤ ሰማይን እንደ ድንኳን የዘረጋ፣ ሦስት ቀን በመቃብር አደረ፤ ከሙታንም ጋር ተቈጠረ፤በሞቱም ሲኦልን በዘበዛት» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፻፺፬-፻፺፭ ቁ.፬-፭)።

ዳግመኛም በዚያው መልእክቱ እንዲህ በማለት አስረድቶአል፤ «በሰማይ በአብ ህልው የምትሆን አንተ ነህ፤ ስለ እኛም በመስቀል የተሰቀልህ አንተ ነህ፤ ዓለም ሳይፈጠር ጀምሮ በጌትነት (በመለኮታዊ) መንበርህ ያለህ አንተ ነህ፤ አሁንም በዕፀ መስቀል ላይ የተቸነከርህ አንተ ነህ፤ በመለኮትህ ሕማም ሞት የሌለብህ አንተ ነህ፤ በሥጋ መከራን የተቀበልህ አንተ ነህ፤ ከአብ ጋር አንድ እንደ መሆንህ፣ በፈቃድህ የሞትህ አንተ ነህ፤ በመቃብር ያደርህ አንተ ነህ፤ በኪሩቤል ላይ ያለህ አንተ ነህ፤ ከሙታን ጋር በመቃብር የነበርክ አንተ ነህ፤ በአንተ ድኅነት ተሰጠ፤ ከሙታን ጋር የተቈጠርክ አንተ ነህ፤ ለሙታንም ትንሣኤን የምትሰጥ አንተነህ፤ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በመቃብር ያደርክ አንተ ነህ፤ በዘመኑ ሁሉ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምትኖር አንተ ነህ፤ በመለኮት ሕማም ሳይኖርብህ በሥጋ የታመምክ አካላዊ ቃል አንተ ነህ» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፻፺፭፣ ቁ.፲፩-፲፫)።

## ጥያቄ፦አካላዊ ቃል ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን በመለኮቱ ታመመ (መከራን ተቀበለ)፤ በመለኮቱ ሞተ ማለት ይገባል?

የለም፤ እንዲህ ማለት አይገባም። ስለዚሁም ቅዱሳን ኦርቶዶክሳውያን አበው የጻፉትን ቀጥለን እንመልከት፦

ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ፣ «እንደ ወንጌል ትምህርት ግን የማይሞተው ሞተ ሊሉ ይገባል፤ በዚህም አነጋገር በመለኮቱ ሕማም፣ ሞት የሌለበት እግዚአብሔር በነሣው ሥጋ ታመመ፣ ሞተ ይባላል» ሲል አስረድቶአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፷፮)። ቀጥሎም ይህ ቅዱስ፣ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ «በመለኮቱ ታመመ፣ ሞተ» ያሉትን ክፍሎች በመገሠፀ እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «ከእኛ በነሣው ሥጋ ሞተ በማለት ፈንታ፣ እግዚአብሔር አምላካችንን ሥጋ በሌለው ባሕርይ ታመመ፣ ሞተ፣ ይሉት ዘንድም ይህን የመሰለ ምን ክሕደት አለ? መለኮት የማይታመም፣ የማይሞት ሲሆን፣ ሕማምን ሞትን ለመለኮት ሰጥተው የተናገሩት፤ ነገር ግን እርሱ (እግዚአብሔር) የታመመ፣ የሞተ በነሣው ሥጋ ነው። ወልድ በመለኮቱ አይታመምም፣ አይሞትም ሊሉ ይገባል፤ ከሥጋ ሳይለይ ከአብ ጋር አንድ ነው እንጂ፤ በሥጋም ቢሆን ከትንሣኤ በኋላ የማይታመምየማይሞት ሆነ» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፷፯)። በተጨማሪም፣ «የመላእክት ጌታ የሚሆን እግዚአብሔር ነፍስን የተዋሐደ ሥጋን ስለ ነሣ (ስለ ተዋሐደ)፣ ከሥጋ ጋርም በተዋሕዶ አንድ አካልአንድ ባሕርይ ሰለ ሆነ፣ ሰውም ሆኖ ስለ ታየ፣ በባሕርየ መለኮቱ ታመመ፣ ሞተ ተብሎ እንደምን ይነገራል? እንዲህ ሳለ ካለ ሥራ ወገን ሊነገርለት አይገባም፤ እንዲህ ብሎ ለሚለምን ወዮለት፤ እጅግ ጽኑ ክህደት ነውና» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፷፯፣ ቁ.፳፯)።

ቅዱስ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘቂሣርያም ሰለ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት በጻፈው መልእክቱ እንዲህ ብሎአል፤ «አሁን ግንእግዚአብሔር ሞተ ሲል ብትስማ አትፍራ፤ የማይሞተውን ሞተ ሊሉ አይገባም ከሚሉ ዕውቀት የሌላቸው ሕማሙን ሞቱን ከሚክዱ መናፍቃን የተነሳ አትደንግጥ። እኛ ግን በመለኮቱ ሞት እንደ ሌለበት፣ በሥጋ ቢሞትም በመለኮቱ ስልጣን እንደ ተነሳ እናውቃለን። ሞት የሌለበት ባይሆንስ ኖሮ በሥጋ በሞተ ጊዜ ሥጋውን ባላስነሣም ነበር፤ ሥጋውም እስከ ዓለም ፍጻሜ በመቃብር በኖረ ነበር» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ ፻፲፰፣ ቁ.፲፯-፲፰)።

ናጣሊስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሮሜም፣ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በመለኮቱ ታመመ፣ ሞተ፣ ብለው ያስተማሩትን ሲያወግዝ እንዲህ ብሎአል፤ «እመቦ ዘይትህበል ወይብል በእንተ እግዚእነ ኢየሱ

ስ ክርስቶስ ከመ ሐመ በመለኮት ወአኮ በሥጋ፣ ኃዲጎ ቃለመጽሐፌ ዘይብል እስመ ክርስቶስ ሐመ በእንቲአነ በሥጋ ውጉዘ ለይኩን፤ ክርስቶስ በሥጋ ስለ እኛ ታመመ የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ትቶ፣ ደፍሮ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ያይደል በመለኮት ታመመ የሚል ቢኖር የተወገዘ ይሁን» ብሎአል።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ቴኦሎጎስ (ነባቤ መለኮት) አፑልናርዮስን በተቃወመበት መልእክቱ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በመለኮቱ ሕማም፣ ሞት ሳይኖርበት በተዋሐደው ሥጋ እንደ ታመመ ሲያስረዳ፣ «በመለኮት ሞት ሳይኖር በሥጋ ሞትን ገንዘብ አደረገ፤ በመለኮት መወሰን ሳይኖርበት በሥጋ ተወስነ፤ የማይመረመር ስማያዊ እርሱ ሥጋን ተዋሕዶ በምድር ተገለጠ፤ የማይታየውታየ፤ በኃጢአት ወድቆ የነበረ የቀደመ ሰው አዳምን ዳግመኛ ያከብረው ዘንድ እግዚአብሔር ፍጹም ሥጋን ነፍስን ተዋሕዶአልና» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፪፻፲፮፣ ቊ.፲፯)።

መለኮት ከሥጋ ጋር በማይመረመር ተዋሕዶ አንድ ከሆነ በኋላ፣ ፍልጠት ማለት መለየት ሳይኖርበት፣ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በተዋሐደው ሥጋ ሲታመምና ሞትን ሲቀምስ መለኮቱ ከሥጋው እንዳልተለየ፣ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ በምሳሌ እንዲህ አለ፤ «ረቂቅ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ባሕርይ የሆነውን ተዋሕዶ አንካድ፤ ብረት ከእሳት ጋር በተዋሐደ ጊዜ ከእሳትም ጋር በመዋሐዱ የእሳትን ባሕርይ ገንዘብ እንዲያደርግ፣ ብረት በመዶሻ በተመታ ጊዜ ከእሳት ጋር በአንድነት እንደሚመታ፣ ግን መዶሻው በተመታ ጊዜ ከእሳት ጋር በአንድነት እንደሚመታ፣ ግን ከመዶሻው የተነሣ የእሳት ባሕርይ በምንም በምን እንዳይጐዳ፣ ቃለ እግዚአብሔር አማኑኤልም በመለኮቱ ሕማም ሳይኖርበት፣ በሥጋ እንደ ታመመ እንዲህ እናስተውል» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፳፻፸፪ ቊ.፲፪)። ከዚያው አያይዞም ይህ ቅዱስ አባት ሲያስረዳ፣ «የተሰቀለው ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ነው፤ ከእርሱም ጋር አንድየሆነ ይህ ቃል በተዋሐደው ሥጋ ሞተ፤ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ የሚያሳርገው መለኮት ግን አልሞተም» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፪፻፸፪፣ ቊ.፲፭)።

አባ ብንያም ሊቀ ጳጳስ ዘእስክንድርያ ደግሞ፣ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በተዋሐደው ሥጋ እንደ ታመመና እንደ ሞተ፣በመለኮት ግን ሞት እንደ ሌለበት እንዲህ ሲል አስረድቶአል፤ «እግዚአብሔር ቃል በሥጋ በእውነት እንደ ታመመ፣ በመለኮቱ ግን ፈጽሞ የማይታመም፣ የማይሞት እንደ ሆነ እንሆ ነገሩ ታወቀ፤ ተረዳ፤ ነገር ግን እርሱ መለወጥ መቀላቀል የሌለበት እንደ ሆነ፣ የባሕርያት አለመቀላቀል ለዘላለሙ ጸንቶ ይኖራል» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፫፻፹፬፣ ቊ.፲፰)።

አባ ብንያም፣ ክርስቶስ በመለኮቱ ታመመ፣ ሞተ፣ ያሉትን ከቅዱሳን አባቶች ትምህርት እየጠቀስ ይመልሳቸው ነበር። በዚሁ መሠረት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያ በታሰረበት ደሴት ሳለ በርጢር ወደ ተባለው ሰው በላከው መልእክቱ፣ «ክርስቶስ በመለኮቱ ታመመ፣ ሞተ» ያሉትን እንዳወገዘ አባ ብንያም መስክሮአል። አባ ብንያም ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ በመልእክቱ እንደ ጠቀሰው፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ የላከው መልእክት በከፊል እንዲህ የሚል ነው። «እኛስ፣ እግዚአብሔር ቃል በመለኮቱ ታመመ፣ ሞተ፣ የሚለውን ሁሉ አውግዘን ልንለየው ይገባናል፤ ከኦርቶዶክስ ሃይማኖታችን አሁን ተለይተዋልና፤ ከጉባኤያችንም ልንለያቸው ይገባናል፤ ከወንድሞቻችን (ከምእመናን) አይደሉምና፤ እንኪያስ አስቀድመን ስማቸውን ከጠራናቸው ከነአርዮስ፣ ከነአፑሊናርዮስ፣ ከነናዳቢደረ ወገኖችም ጋር ይህን አንድ ክሕደት ይናገራሉ፤ እነዚህም እርስ በርሳቸው በክሕደት የተያያዙ፣ የሚመሳሰሉ ናቸው፤ የነናዳቢስ ወገኖችም መለኮት ከሥጋ ጋር በአንድነት ታመመ ይላሉ፤ እኛ ግን እንዲህ ብለን እናምንም፤ እግዚአብሔር ቃል በእውነት ሥጋን እንደ ተዋሐደ፣ በመለኮቱ ግን ፈጽሞ ሕማም፣ ሞት ያሌለበት እንደሆነ እናምናለን እንጂ፤ አእምሮ በማጣታቸው ክርስቶስ በመለኮት ያይደለ በሥጋ ታመመ ብለን በዚህ አነጋገር በኬልቄዶን ከተሰበሰቡ «መናፍቃን» ጋር አንድ ሆነን እንገኛለን የሚሉ አሉ፤ እኛም ቅዱስ ቄርሎስ፣ (እነርሱ እንደሚገባ ብዙ ነገር ያምናሉና ከሕደታቸው እንራቅ እንጂ መናፍቃን ከሚናገሩት ሁሉ ፈጽመን ልንርቅ አንች^ልም) ብሎ ጽፎአል፤ ብለን እንመልሰላቸዋለን፤ የኬልቄዶን ማኅበር ወገኖች እግዚአብሔር ቃል በመለኮት ያይደለ በሥጋ እንደ ታመመ ካመኑ፣ እኛም በዚህ ነገር ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ ሁለት ባሕርይ ካሉ፣ አንድ ወልድንም ወደ ሁለት አካል ከከፈሉት ሁለትም ካደረጉት ግን በዚህ ከእነርሱ ጋር አንተባበርም» ሲል አስረድቶአል (ሃይማኖተ አበው አባ ብንያም፣ ገጽ.፫፻፹፯-፫፻፹፰፣ ቊ.፴፮-፴፯)። ቅዱስ ቴኦዶስዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያም፣

«እግዚአብሔርም ቃል ስለ እኛ በሥጋ እንደ ታመመ ካላመንስ ሃይማኖታችን ከንቱ ነው...» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፫፻፺፩፣ ቍ.፲፰)።

መለኮት ከትስብእት ጋር ያለመለወጥ፣ ያለመቀላቀል፣ ያለመለየት በተዋሕዶ አንድ ስለሆነ፣ ወልድ ዋሕድ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፣ በመለኮቱ ሕማም፣ ሞት ሳይኖርበት በተዋሐደው ሥጋ እንደ ታመመና እንደ ሞተ፣ በመለኮቱ ሞትን ድል አድርጎ ከሙታን ተለይቶ እንደ ተነሳ ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋግጣሉ። ከዚሁ ጋር ክርስቶስ በሥጋው መከራ መስቀልን ተቀበለ ቢባልም፣ ቅዱስ ቄርሎስ በእሳትና በብረት መስሎ እንደ ተናገረ፣ መለኮት ምን ጊዜም ለቅጽበት ያህል እንኳ ከተዋሐደው ሥጋ አልተለየም፤ የተፈጸመው ተዋሕዶ ያለመለየት ነውና። መለኮቱ በሕማም፣ በሞት ጊዜ ተለየው ማለት ዐቢይ ክህደት ነው።

## ጥያቄ፦በጥንት ዘመን፣ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ድካም፣ ሕማም፣ ሞተ የማይስማው ልዩ የሆነ ሥጋ ነበር ብለው ያስተማሩት መናፍቃን ተነስተው ነበር ይባላል፤ ይህ እውነት ነውን?

አዎን፤ እውነት ነው። «ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ከስማይ የወረደ ልዩ ፍጥረት የሆነ ሥጋ ነው፤ ስለዚህም የሰውን ሥጋ የመሰለ ነበር እንጂ በእውነት (በእርግጥ) ከማርያም የተወሰደ የሰው ሥጋ አልነበረም፤ ግን የሚያየው የሰው ሥጋ ይመስል ነበር» ብለው ያስተማሩት መናፍቃን ተነስተው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ፣ በተመሳሳይ መንገድ ሌሎች መናፍቃን ተነስተው ነበር። እነርሱም፣ «ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ከቅድስት ማርያም የተወሰደ የሰው ሥጋ ነበር፤ ነገር ግን ከመለኮት ጋር ሲዋሐድ እንደ መለኮት ድካም፣ ሕማም፣ ሞት ነበር» ብለው ያስተማሩ መናፍቃን ተነስተው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ፣ በተመሳሳይ መንገድ ሌሎች መናፍቃን ተነስተው ነበር። እነርሱም፣ «ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ከቅድስት ማርያም የተወሰደ የሰው ሥጋ ነበር፤ ነገር ግን ከመለኮት ሲዋሐድ እንደ መለኮት ድካም፣ ሕማም፣ ሞት የማይስማው፤ መብል፣ መጠጥ የማይስማማው ልዩ ሥጋ ሆነ፤ለሚያየው ግን የሚበላ፣ የሚጠጣ፣ የሚታመም፣ የሚደክም መስሎ ይታይ ነበር» ብለው ያስተምሩ ነበር።

የሁለቱም ክፍሎች ኑፋቄ ተመሳሳይ ነው፤ የመጀመሪያዎቹ፣ «የክርስቶስ ሥጋ ከስማይ የወረደ ልዩ ሥጋ ነው» ሲሉ፣ በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሱ መናፍቃን ደግሞ፣ «ክርስቶስ ከቅድስት ማርያም የነሣው ሥጋ በውላጤ (በመለወጥ) ልዩ ሥጋ ሆነ» ብለው አስተማረዋል። ስለዚህ ሁለቱም ክፍሎች፣ «የክርስቶስ ሰውነት ወይም ሥጋው የሰው ሥጋ መስሎ ታየ እንጂ በእርግጥ የሰው ሥጋ አልነበረም» ብለዋል ማለት ነው። በዚሁ መሠረት የነዚሁ መናፍቃን ትምህርተ ሥጋዌ በጽላሎት፣ በምትሐት የተመሠረተ ነው። ስለዚህ ትምህርታቸው ምትሐት፣ ጽላሎት ይባላል። በግሪክ ዶኬቲዝም ሲባል፣ እነርሱ ደግሞ ዶኬቲስቶች (ዶርቲሰተሰ) ይባላሉ። አስመሳዮች መተተኞች ማለት ነው።

እነዚህ መናፍቃን አስቀድሞ በዘመነ ሐዋርያት ብቅ ብለው ስለ ነበር፣ ስለ እነርሱ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ምእመናኑን በማስጠንቀቅ ሲጽፍ፣ «ስለ ሕይወት ቃል ከመጀሪያ የነበረውንና የሰማነውን፣ በዓይኖቻችንም ያየነውን፣ የተመለከትነውንም፣ እጆቻችንም የዳሰሱትን እንናግራችኋለን »ብሎአል (፩ዮሐ.፩፥፩-፫)። በተጨማሪም ይህ ቅዱስ ሐዋርያ ሲያስረዳ፣ «ወንድሞቼ ሆይ፤ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና፤ የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው፤ ይህም እንደሚመጣ ሰምታችኋል፤ አሁንም እንኳን በዓለም አለ» ብሎአል (፩ዮሐ.፬፥፩-፬)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፣ «ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ከስማይ ይዞት የወረደው ነው» ያሉትን መናፍቃን በማሳፈር፣ በባርነት ታስረው የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ፤ የአብርሃምን ዘር ነስቶአል እንጂ፣ የነሣው የመላእክትን አይደለም» ሲል አስተምሮአል (ዕብ.፪፥፲፬-፲፮)።

ሐዋርያው እንዳለው፣ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ ከስማይ የወረደ ሳይሆን የአብርሃምና የዳዊት ዘር ከሆነችው ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው ነው፤ ይኸውም «ከኃ

ጢአት በቀር በነገር ሁሉ ወንድሞቹን (እኛን) ሊመስል ተገባው» ሲል ሐዋርያው አስረድቶአል (ዕብ.፪፥፲፯)። «በሁሉም ወንድሞቹን መሰለ» ማለቱ፣ ክርስቶስ ከኃጢአት በቀር እንደ እኛ ፍጹም ሰው ሆነ ሲል ነው። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ክርስቶስ የተዋሐደው ሥጋ አማን በአማን የሰው ሥጋ እንደሆነ፣ በምትሐት፣ በጽላሎት ሥጋን መስሎ የታየ ማለት ሳይሆን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተገኘና ያለ መለወጥ ከመለኮት ጋር አንድ የሆነ ሥጋ መሆኑን አስረድቶአል ።ቅዱስ አግናጥዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘአንጾኪያ፣ ዶኬቲስቶችን በማሳፈር ሲያስተምር፣ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት ተወለደ፤ በእውነት አደገ፤ በእውነት በላ፤ ጠጣ፤ በእውነት ተሰቀለ፤ በእውነት ታመመ፤ ሞተ፤ ተቀበረ፤ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ ይህንን ያመነ ብፁዕ ነው፤ ይህንን የካደ ግን እኛተሰፋ ከምንደርጋት ከተባረከች ሕይወት የተለየ ነው» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው ፣ገጽ.፴፱ ቍ.፪-፫)።

ሰማዕት እየተባለ የሚጠራው የሮሙ ሊቀ ጳጳስ ፊሊክስም፣ ወልደ እግዚአብሔር የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ከኃጢአት በቀር እንደ እኛ እንደሆነ ሲመስክር፣ «ወኢኮነነ ክርስቶስ እጎወ በግብር ሐዲስ፤ አላ በለቢስ ሥጋ ዚአነ በተዋሕዶ ዘኢይትነገር፤ ክርስቶስ በሐዲስ ግብር (በኅድረት፣ በውላጤ) እንደ እኛ ሰው አልሆነም፤ በማይመረመር ተዋሕዶ ባሕርያችንን ባሕርይ አድርጎ ነው እንጂ» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፻፴፭ ቍ.፭)።

በአራተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የነበረው ዮሐንስ ዘኢየሩሳሌም፣ በዘመኑ የነበሩትን መናፍቃን (ዶኬቲስቶችን) በመቃወም የጻፈው እንዲህ የሚል ነው፤ «ከእርሷ (ከቅድስት ማርያም) ሥጋን፣ ነፍስን በተዋሐደ ጊዜ እኛን መሰለ፤ በሐሰት ያይደለ በእውነት ስለ እኛ መከራን ወድዶ ተቀበለ፤ መንገድ በመሄድ እንደ እኛ ደከመ፤ በሐሰት አይደለም፤ በገረፉትም ጊዜ ስለ እኛም ከጲላጦስ መከራን በተቀበለ ጊዜ እንደ እኛ መከራው፣ ግርፋቱ ይሰማው ነበር፤ ፊቱን በጻፉት ጊዜ፣ እጁን እግሩን በችንካር በቸነከሩት ጊዜ የተቀበለው መከራ ይሰማው ነበር» ብሎአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፻፳፯ ቍ.፭-፯)።

በተጨማሪም ይህ አባት እነዚያ፣ «የክርሰቶስ ሰውነት፣ ሕማሙንና ሞቱን ምትሐት ነው» ያሉትን መናፍቃን ሲያወግዝ እንዲህ ብሎአል፤ «በሐሰት ያይደለ በእውነት የሥጋን ሕማም እንደ ታመመ በዚህ እናምናለን፤ (በገረፉት ጊዜ አልተሰማውም፤ በሰቀሉትም ጊዜ አልደከመም (አልረስማውም)፣ በችንካርም በቸነከሩት ጊዜ ሕማም አላገኘውም) ብለው ስለ እርሱ የሚናገሩትን ግን መናፍቃን እንደ መሆናቸው እኛ እናወግዛቸዋለን» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፻፳፰ ቍ.፲)።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ቴኦሎጎስ «ነባቤ መለኮት) ዶኬቲስቶችን በማሳፈር ሲጽፍ፣ «ወኢሐመ እግዚእነ ክርስቶስ፣ በምትሐት አመ ርኅበ ወአመ ጸምአ ወአመ ደክመ በሐዊረ ፍኖት፣ በከመ ይቤሉ ርኩሳን ሰብእ፤ አላ ሐመ በሥጋ እሙነ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራበ፣ በተጠማ፣ መንገድም በሄደ፣ በደከመ ጊዜ በሐሰት መከራ አልተቀበለም፤ የተጠሉ የተነቀፉ ሰዎች እንደ ተናገሩ፤ ነገር ግን በእውነት መከራ ተቀበለ እንጂ» በማለት አስረድቶአል (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፪፻፲፫ ቍ.፳፭)።

**ጥያቄ፦ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በመለኮት፣ በባሕርይ፣ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ በመሆኑ ፍጹም አምላክ ነው፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን፣ ነፍስን ተዋሕዶ ከኃጢአት በቀር ፍጹም ሰው ስለሆነ፣ በሰውነቱ ከእኛ ጋር አንድ ነው። ታዲያ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ይህንን አስመልክተው የተናገሩት ነገር አለን?**

አዎን፤ በብዙ ቦታ በርከት ያለ ምስክር አለ። የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በመለኮቱ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ መሆኑን፣ በሰውነቱም ከኃጢአት በቀር ከእኛ ጋር አንድ መሆኑን፣ በየመልእክቶታቸው በሰፊው ገልጸውታል።

ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ለሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስ ዘአንጾኪያ በጻፈው መልእክቱ እንዲህ ብሎአል፤ «እርሱ (ወልድ) በመለኮቱ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው፤ (ትክክል ነው)፤ እርሱ ራሱም ሰው በመሆኑ ከእኛ ጋር አንድ ነው፤ ሁለቱም ባሕርያት በተዋሕዶ አንድ ሆኑ» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፪፻፴፪)። ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ይህንን ትምህርት ሲያብራ

ራ እንዲህ ብሎአል፤ «በሥላሴ ምንም ምን አልተጨመረም፤ እርሱ አንድ ነውና፤ እርሱ አም ላክ በተዋሐዶ ሰው የሆነ እርሱ ነው። በባሕርየ መለኮቱ ከአባቱ ጋር አንድ ነው፤ እርሱ በሥጋ ባሕርይም ከእኛ ጋር አንድ ነው፤ ሰማያዊ እርሱ ነው፤ ምድራዊም እርሱ ነው፤ እርሱ ይታያል ፤ አይታይም፤ እርሱ ይዳሰሳል፤ አይዳሰስም፤ እርሱ ይወሰናል፤ አይወሰንም፤ እርሱ ይታመማል ፤ አይታመምም» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፫፻፺፫ ቊ.፳፮)።

ቀጥሎም በዚያው መልእክቱ ክርስቶስ በሰውነቱ ከእኛ ጋር አንድ መሆኑን በመግለጽ እንዲህ ብ ሎአል፤ «እኛ ግን አእምሮ የሌላቸው፣ ተዋሕዶን የዘነጉ እነዚህን እንቃወማለን፤ ሥጋን የተዋሐ ደ እርሱም በሥራው ሁሉ እኛን እንደሚመስለን እንናገራለን፤ እኛም ከኃጢአት በቀር ወንድሞ ቹ ነን፤ ከእኛም ጋር አንድ ባሕርይ ሆነ፤ በዚህ ተዛምዶም ከእኛ ጋር አንድ ነው፤ በሕማም ይ መስለናል፤ እርሱ ኃጢአት ከሌለበት ከባህርያችን የተነሣ ጥምን፣ ድካምን፣ እንቅልፍን፣ ይህን የሚመስለውንም ሁሉ ተቀብሎልናል» (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፫፻፺፭ ቊ.፴፪)።

ከዚህ በላይ ባለው ጥቅሱ፣ ሊቁ፣ «አእምሮ የሌላቸው፣ ተዋሕዶን የዘነጉ እነዚህን እንቃወማለ ን» ያላቸው የዶኬቲስቶች ተከታዮች የሆኑትን ማኒንና አውጣኪን ነው። እንደሚታወቀው፣ ማኒ የተባለው መናፍቅ በሦስተኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ላይ ተነስቶ በመካከለኛው ምሥራቅ በክ ሕደቱ የሐዋርያትን ቤተክርስቲያን ያስቸገረ ሰው ነበር። በዘመነ ብሉይ የነበረው ማኒ «አልቦ እ ግዚአብሔር»፣ «እግዚአብሔር የለም» ብሎ ካደ፤ እንዲህም ብሎ በማስተማሩ፣ «ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል» ብለው አበው ነቅፈውታል (መዝ.፲፫(፲፬)፥፩)። ይህ (ሁለተኛው) ማኒ ደግሞ፣ «የክርስቶስ ሰውነት ረሃብ፣ ጥም፣ ሞት የሚሰማው አልነበረም፤ ስለዚህ ክርስቶስ የተራበ፣ የተጠማ፣ የበላ፣ የደከመ፤ የታመመ መስሎ ታየ እንጂ በእውነት (በእርግጥ) አልተራበ ም፤ አልተጠማም፤ አልደከም፤ አልታመመም» ብሎ ያስተምር ያስት ነበር።

አውጣኪም፣ «ክርስቶስ ከተዋሕዶ በኋላ በሰውነቱ (በሥጋው) ከእኛ ጋር አንድ አልነበረም። ስለ ዚህ ክርስቶስ በመለኮቱ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ (ኅቡረ ህላዌ) ቢሆንም፣ በሰውነቱ ( በሥጋው) ከእኛ ጋር አንድ ባሕርይ (ኅቡረ ህላዌ) አይደለም» ብሎ አመነ፤ በዚሁ እምነቱ አው ጣኪ፣ «ከተዋሕዶ በኋላ የክርስቶስ ሰውነት ተለወጠ፤ መለኮት ሰውነቱን ለወጠው፤ መጠጠው» ብሎ እንዳመነና እንዳስተማረ ስለ ታወቀ፣ በዘመኑና በኋላም በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተወግ ዞአል። በክሕደት የአውጣኪ አያት የነበረውን የሦስተኛውን ክፍለ ዘመን ማኒንም የቤተክርስቲያ ን ሊቃውንት ደጋግመው አውግዘውታል።

ማኒ በ፪፻፲፮ዓ.ም በባቢሎን አገር፣ በባግዳድ ከተማ አጠገብ ተወለደ። በከፊል የአረማውያንን ትምህርት (እምነት) እንደ ያዘ የክርስትናን ሃይማኖት ተቀብሎ ክርስቲያን ሆነ። በዘመኑ ይደረጋ ሉ ተብለው በተገመቱት ነገሮች ላይ ማኒ የሐሰት ትንቢት ይናገር ስለነበር፣በተከታዮቹ ዘንድ «ነ ቢዩ ማኒ» እየተባለ ይጠራ ነበር። ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የነበረውን እምነት እንደ ዘሮአስት ሪያኒዝም (Zoroastrianism) ያለ የዱአሊዝም እምነት ነበር፤ በመንታ አማልክት ማመን ማለት ነ ው። ስለዚህ ማኒ ክርስቲያን ከሆነ በኋላ፣ ቀደም ብሎ ይዞት የነበረው  የዱአሊዝም እምነት ከልቡ ሊጠፋ አልቻለምና በሁለት አምላክ ማለት «አምላከ ብርሃን፣ አምላከ ጽልመት» እያለ ያምን ነበር። በዚሁ እምነቱ መሠረት ማኒ (ማንክዮስ) ክርስቶስ አምላከ ብርሃን ብሎ ያመልክ ው ነበር። በተጨማሪም ማኒ በትምህርቱ «መናፍስት ቅዱሳን ናቸው፤እግዚአብሔር መንፈስ ስለ ሆነ ቅዱስ ንጹሕ ነው፤ ሥጋ (ማተር) ግን ርኩስ ነው» እያለ ያስተምር ነበር። እንደ ማኒ ትም ህርት፣ «ነፍስ እንጂ ሥጋ ንጹሕ አይደለም፤ ነፍስ በአምላከ ብርሃን ስለ ተፈጠረች ንጽሕት ቅ ድስት ናት፤ ሥጋ ግን በአምላከ ጽልመት ሰለ ተፈጠረ ርኩስና ሰይጣን ነው። ማኒ፣ «አምላከ ብርሃን እየተባለ የሚጠራው ክርስቶስ ንጹሕ መንፈስ ስለሆነ አማናዊ የሆነውን ሥጋ አልለበሰም ፤ እንደ ማንኛውም ሰው ሁሉ ፍጹም ሰው አልሆነም፤ በማስመሰል፣ በምትሐት ሥጋን የመሰለ ለበሰ፤ በመካከላችን ተመላለሰ... » እያለ ያስተምር ነበር፤ ማኒ በዚህ የጽላሎትና የምትሐት ት ምህርቱ ዶኬቲስት ከተባሉ የግኖስቲክ (Gnostic) ወገን መናፍቃን ጋር ይመሳሰላል። ዶኬቲስቶች ም ልክ እንደ ማኒ፣ «ክርስቶስ በምትሐት፣ በመምሰል ሰው ሆነ እንጂ አማናዊ ሰው አልሆነም » እያሉ ያስተምሩ ነበር። ተከታዮቹም መነናውያን (Manichaeism) ይባላሉ። ማኒይዝም እስከ ፮ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ በኢራን፣ በኢራቅ፣ በህንድና በሰሜን አፍሪካ ተሰፋፍቶ ነበር።

የሰሜን አፍሪካ ተወላጅ የነበረው አውግስቲኖስም በፊት የማኒይዝም እምነት ተከታይ እንደ ነበር ታሪክ ይናገራል። በዶኬቲዝምና በማኒዝም ትምህርት መሠረት ምስጢረ ሥጋዌ ምትሐት፣ ጽላሎት እንጂ አማናዊ (ተጨባጭ) አይደለም። ሁለቱም ወገኖች ያስተማሩት ትምህርት፣ «ክርስቶስ የለበሰው ሥጋ በአርአያው የእኛን ሥጋ ይምስል እንጂ እውነተኛ (አማናዊ) ሥጋ አልነበረም፤ ስለዚህ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነበር እንጂ ፍጹም ሰው አልሆነም፤ ክርስቶስ ለሚመለከተው ሰው፣ የበላ፣ የጠጣ፣ የደከመ መስለ እንጂ በእርግጥ አልተራበም፤ አልተጠማም፤ አልደከመም፤ በጌቴሴማኒ ዐጸድ በጸሎቱ ጊዜ የፈራ መስለ እንጂ አምላክ ሰለሆነ አልፈራም፤ እንደዚሁም ያዘነ፣ የተከዘ መስለ እንጂ አምላክ ስለሆነ አላዘነም አልተከዘም» የሚል ነበር። በዚሁ እምነቱ መሠረት ማኒ (ማንክዮስ) የመናፍቃን አባት እየተባለ ይጠራል።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት መናፍቃን ጋር በመናፍቅነት የሚዛመድ ደግሞ አቡሊናርዮስ ነው። እርሱም ከ፫፻፲-፫፻፺ ዓ.ም የነበረ፣ ለተወሰኑ ዓመታት የሎዶቅያ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ በዚያ የነበረችውን ቤተክርስቲያን የመራ ሰው ነበር። በምስጢረ ሥላሴና በምስጢረ ሥጋዌ ትምህርት አቡሊናርዮስ የእስክንድርያን አቅዋም የሚከተል ምሁር እንደ ነበር የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ይመሰክሩለታል። በዚሁ አቋሙም ከቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረው ይባላል። በዚሁ መሠረት ቅዱስ አትናቴዎስ በኒቅያ ከተማ ስለ ተወሰነው የሃይማኖት ውሳኔ ከአርዮሳውያን ጋር የከረረ ትግል ባካሄደበት ወቅት፣ አቡሊናርዮስም ቀኖና ሃይማኖትን (ጸሎተ ሃይማኖትን) በሚመለከት «አሙኡስዮስ (ወልደ ኅቡረ ህላዌ ምስለ አብ)» የሚለውን የኦርቶዶክሳዊ ትምህርት የሚደግፍ እንደ ነበር የነገረ መለኮት ታሪክይመሰክርለታል።

ነገረ ክርስቶስ (ምስጢረ ሥጋዌን) በሚመለከት ደግሞ አቡሉናርዮስ እንደ እስክንድርያውን ሊቃውንት አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ (ሚአፊሲስ፤ ኤን ኤኖሲስ) የሚለውን የተዋሕዶ ሃይማኖት አቋም የሚከተል ስለ ነበር፣ እድሜ ልኩን የአንጾኪያውያንን የምንታዌ (የዱአሊዝም) ትምህርት በጥብቅ በመቃወም ትግል ሲያካሄ ኑሮአል። በዚህ ዓይነት አንዱን ክርስቶስ ከሁለት በመክፈል፣ «የእግዚአብሔር ልጅና የማርያም ልጅ በመስተፃምር (በሰኒአፍያ) አንድ ሆኑ እንጂ ኢየሱስ በባሕርይ የማርያም ልጅ እንጂ የእግዚአብሔር ልጀ አይደለም» ብለው ያስተማሩትን የጳውሎስ ሳምሣጢር ደቀ መዛሙርት አቡሊናርዮስ በጥብቅ ያወግዛቸው ነበር።

ነገር ግን አቡሊናርዮስ በአንድ በኩል ለተዋሕዶ ሃይማኖት የቆመ ቢመስልም፣ በሌላ በኩል ግን ምስጢረ ሥጋዌን ከፍልስፍና ትምህርት፣ ማለት ከአዲሱ የፕላቶን (Neoplatonism) ፍልስፍና ጋር ለማዛመድ ሲሞክር ከከፋ የኑፋቄ (ክሕደት) ማጥ ሊዘፍቅ ቻለ። ትምህርቱም እንዲህ የሚል ነበር፤ «አካላዊ ቃል ፍጹም ጥበበኛ የነፍስ ፈጣሪ ስለሆነ፣ ለባዊት ነፍስን ለሰው ልጅ የሚያድል በመሆኑ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን በለበስ (በተዋሐደ) ጊዜ ደማዊት ነፍስን (ደመ ነፍስን) ነሣ (ተዋሐደ) እንጂ፣ ለባዊት፣ ነባቢት (የማታውቅና የምታስብ) ነፍስን አልነሣም (አልተዋሐደም)፤ ነገር ግን መለኮቱ (አምላክነቱ) እንደ ለባዊነትና ነባቢት ነፍስ ሆነለት፤ ስለዚህ አካላዊቃል በራሱ ፍጹም ስለሆነ ፍጹም የሆነ ባሕርየ ሰብእን አልተዋሐደም.. » እያለ ያስተምር ነበር። የቤተክርስቲያን አባቶች በሙሉ የአቡሊናርዮስን ትምህርት አጥብቀው ተቃውመዋል። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስን ትምህርት አጥብቀው ተቃውመዋል። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ፣ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያና ሌሎችም የአቡሊናርዮስን ትምህርት በመቃወምና በማውገዝ መጻሕፍት ጽፈዋል። በተለይም፣ «መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ አይደለም» ያሉትን መናፍቃን ለማውገዝ በቁስጥንጥንያ የተሰበሰቡት ቅዱሳን አባቶች በ፫፻፹፩ዓ.ም አቡሊናርዮስን ናትምህርቱን አውግዘዋል።

ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ከሚለው አቡነ ገብርኤል በ1991 ካሳተሙት የተወሰደ።